የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE
# OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ ጥር ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24rd Year, No. 19
ADDIS ABABA, 20thJanuary, 2018

**ማውጫ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፪/፪ሺ፲ዓ.ም

የብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………….ገጽ ፲ሺ፷፩

**CONTENT**

Council of Ministers Regulation No.422 /2018

National Animal Genetic Improvement Institute Establishment Council of Ministers Regulation……………………………………page 10061

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፪/፪ሺ፲

**ብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፴፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፪/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "እንስሳት" ማለት የምግብ ምርትና የጭነት ወይም ተቀጽላዎችን የመጎተት ኃይል መስጠት የሚችሉ ለማዳ እንስሳት ሆኖ የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ግመል፣ ዶሮ፣ ዓሳማ፣ የጋማ ከብት እና ጥንቸል፣ የመሳሰሉትን ያካትታል፤

፪/ "የእንስሳት ምርት" ማለት ከእንስሳት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚገኝ ለሰው ወይም ለእንስሳ ፍጆታ የሚውል፣ ወይም ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚዉል ሥጋ፣ ወተት፣ ማር፣ ቅቤ፣ ዕንቁላል፣ ፀጉር፣ ቆዳ እና ሌጦ ወይም የጭነት ወይም ተቀጽላዎችን የመጎተት ኃይል እና የመሳሰሉትን ይጨምራል

፫/ "ዝርያ" ማለት ተመሳሳይ ውጫዊ እና ውስጣዊ ወይም የጀኔቲክስ ባህርያት ያላቸውና እነዚህንም ባህርያት በተከታታይ ውልደት ማስተላለፍ የሚችሉ የእንስሳት ስብስብ ነዉ፤

፬/ "አባላዘር" ማለት በሰው ቴክኒካዊ አሠራር ከርቢ ኮርማ ተሰብስቦና በላቦራቶሪ ተቀነባብሮ በቀሰም ዉስጥ የታሸገ የወንዴ ዘር ሲሆን፣ በሰው ቴክኒካዊ አሠራር ከርቢ ኮርማ ተሰብስቦ በላቦራቶሪ ሳይቀነባበርና በቀሰም ዉስጥ ሳይታሸግ ወዲያዉ አገልግሎት ላይ ሊዉል የሚችል የወንዴ ዘርንም

Council of Ministers Regulation 422/2018

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL ANIMAL GENETIC IMPROVEMENT INSTITUTE THE NATIONAL**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 38 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.916/2015

**1.Short Title**

This Regulation may be cited as the "National Animal Genetic Improvement Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 422/2018"

**2. Definition**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/"Animal" means domesticated animal that can produce food items and used for draught/traction power and includes cattle, sheep, goat, camel, chicken, pig, equines, rabbit and other similar animals;

2/ "Animal product" means a products that is obtained directly or indirectly from animals for human or animal consumption, or for industrial inputs and includes meat, milk, honey, butter, eggs, hair, hide, skin, pack or traction draught power and other similar products;

3/ "Breed" means a group of animals that have common phenotypic and genotypic characteristics, can be transmitted to the next generations;

4/ "Semen" means an ejaculate collected artificially from male reproductive tract and processed and packed in straws; it also includes a fresh ejaculate collected artificially from male

ያጠቃልላል፤

፭/ "ሽል" ማለት የሴቴ እንቁላልና የወንዴ አባላዘር በመዋሃድ ሕይወት ለማፍራት ጅምር ላይ የደረሰ ሆኖ ከሴቴ ማህጸን የሚሰበሰብ ጽንስ/ሽል ነው፤

፮/ "የለማ እንቁላል" ማለት የወንዴና ሴቴ ዘር በመዋሃድ ወደ ሽል ሊለወጥ የሚችል እንቁላል ነዉ፤

፯/ "ማዳቀል" ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዝርያዎችን በማገናኘት የተሻለ ምርታማ የእንስሳት ዝርያ የሚገኝበት ዘዴ ነው፤

፰/ "የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ" ማለት በመረጣ ወይም በማዳቀል ወይም በሁለቱ ዘዴ በመጠቀም የሚደረግ የእንስሳት ምርታማነት የማሻሻል አሠራር ነዉ፤

፱/ "የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት" ማለት ሥነ-ህይወታዊና ቴክኒካዊ ቁሶችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚጠቀሙ እንደ ርቢ ቁም እንስሳት፣ አባላዘር፣ ሽል፣ የለማ እንቁላል እና የሥነ-ተዋልዶ ቁሳቁሶችን የሚያጠቃልል ይሆናል፤

፲/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነዉ፤

፲፩/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ ሴትንም ይጨምራል፡፡

**፫.መቋቋም**

፩/ ብሔራዊ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

**፬.ዋና መስሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡

**፭.ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዓላማ የእንስሳት ዝርያዎችን በማሻሻል፣ ዘላቂ የዝርያ አቅርቦት በማስፋፋትና የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ በማገዝ የአርቢውን ህብረተሰብና የሀገሪቱን ብሔራዊ ገቢ በማሳደግ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ማምጣት ይሆናል፡፡

**፮.የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የእንስሳት ዝርያዎችን ለማሻሻል፣ ዘላቂ የዝርያ አቅርቦት ለማስፋፋትና የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ለማገዝ የሚረዱ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል ለቴክኖሎጂ ሽግግር ይሰራል፤

፪/ ብሔራዊ የእንስሳት የርቢ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ በመንግስት ሲፀድቅም በኃላፊነት ይፈጽማል፣ የክልሎችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

reproductive tract to be used immediately;

5/ "Embryo" means a fertilized egg by spermatozoon collected from female reproductive tract (uterus);

6/ "Fertile egg" means cells resulting from the union of ovum and spermatozoon that develops to embryo;

7/ "Cross breeding" means mating of two or more different breeds to obtain improved genotypes;

8/ "Breed improvement" means enhancement of animal productivity through selection, cross breeding or both;

9/ "Breed improvement input" means biological or technical equipment employed to develop products and productivity and includes live breeding animals, semen, embryo, fertile egg, and reproduction equipment;

10/ "Minister" and "Ministry" means the Minister and Ministry of Livestock and Fisheries Resource, respectively;

11/ Any expression in the masculine gender includes the feminine

**3 . Establishment**

1/ The National Animal Genetic Improvement Institute (hereinafter referred as the "Institute") is here by established as an autonomous Federal Government Institute having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

**4. Head Office**

The Institute shall have its head office in AddisAbaba and may have branch offices elsewhere, as maybe necessary.

**5. Objectives**

The main objectives of the Institute shall be to increase production and productivity of animals, and there by ensure increased farmers income and economic transformation of the country through breed improvement and continual supply of improved animal genotype

**6. Powers and Duties of the Institute**

The Institute shall have the following powers and duties:

1/ Undertake research and study on increasing production and productivity of animals through breed improvement and continual supply of improved animal genotype, work towards technology transfer.

2/ Prepare national breeding policy, programs and strategy; implement same upon approved by the Government and follow up their implementation at regions;

፫/ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት ወደ ሀገር በማስገባትና ሀገር ውስጥም በማምረት፣ በማባዛት አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፬/ ለአባላዘር ማቆያ ባንክና ለመስክ አገልግሎት የሚሆን ፈሳሽ ናይትሮጂንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በበቂ መመረቱንና መኖሩን ያረጋግጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፭/ በሀገር አቀፍ ደረጃ የዝርያ ማሻሻያ ዕቅድ ያወጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፮/ የዝርያ ማሻሻያ አገልግሎት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ወጥ የሆነ ሀገራዊ የእንስሳት ብዜት ሪከርድ አያያዝ ሥርዓትና የመረጃ ቋት እንዲሁም ድረገጽ ያደራጃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፯/ የመረጃ ትንተናና ሥርጭት አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመዘርጋት የዝርያ ማሻሻያ ዉጤት በምርት ግኝት፣ የባህርያት ለዉጥ የልኬትና ምዝገባ ሥርዓት ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች በመረጃ ሥርጭትና ቅብብሎሽ ሂደትና ግብረ-መልስ ይከታተላል፤

፰/ ለእንስሳት ዝርያ መሻሻል አስተዋጽዎ የሚያደርጉ የእንስሳት ብዜት ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፤ በእንስሳት ዝርያ መሻሻል ዙሪያ መንግሥትን ያማክራል፡፡

፱/ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን በብዙሀን መገናኛ፣ በድረገፅ፣ በበራሪ ጽሁፎች፣ ፖስተሮችና ሌሎች ትምህርት ሰጪ መልዕክቶችን ያሰራጫል፣ የተገኘውንም ውጤት ይከታተላል፤

፲/ በዝርያ ማሻሻያ ተግባራት የተቋሙንና የሌሎች ባለድርሻ አካላት የሥራ እንቅስቃሴ ትስስር ሥርዓት በመዘርጋት የተገኘውን ውጤት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፲፩/ በእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ተግባራት ላይ ለተጠቃሚዎች ሥልጠናዎች ይሰጣል፤ አውደ ጥናት፣ ሲምፖዚዬምና ሴሚናሮችን ያዘጋጃል፤ በእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ተግባራት ላይ በሚሳተፉ የተለያዩ አካላት መካከል የልምድ ልዉዉጥ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

፲፪/ የእንስሳት ሀብት ምዝገባ፣ ዝውውር፣ ልውውጥና አጠቃቀም ላይ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት እንዲከናወን ያደርጋል፤

፲፫/ ከእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓቶችና መሣሪያዎች ሽያጭ በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የወጪ መሸፈኛ ገቢ ይሰበስባል፤

፲፬/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፭/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፣ ፲ሺ፷፬

፪/ በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና

3/ Import and domestically produce and breed quality and standardized breed improvement inputs and ensures their appropriate supplies;

4/ Ensure sufficient availability of liquid nitrogen and other necessary breeding inputs for semen preservation in semen banks, for field operation purposes and follow up its execution;

5/ Design national animal breeding plan and follow up its implementation;

6/ Collect breed improvement data, establish natial animal breed recording system, set up database,develop webpages and follow up its implementation;

7/ Process data and analyses the impact of breed improvement on genetic gain, productivity and give advices and feedback to users;

8/ Establish, organize and lead animal breeding centers that contribute for genetic improvement; provide advice to Government on genetic improvement;

9/ Disseminate breed improvement activities on public media, webpages, fliers, posters and through other knowledge sharing means and follow up its outcome;

10/ Establish synergy between the Institute and other stake holders and report the output to the concerned body, give technical support;

11/ Provide technical trainings for beneficiaries improved breed; organize workshops, symposia and seminars concerning animal breed improvement, facilitate experience sharing programs among stakeholders involved in animal breed improvement;

12/ Lead animal resources registration, movement, exchange and uses in consonance with international conventions;

13/ Collect cost recovery fees from proceeds of breed improvement inputs pursuant to the rate determined by the Government;

14/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

15/ Perform other related activities necessary for the attainment of its objective

## 7.<u>Organization of the Institute</u>

The Institute shall have:-

1/ An Advisory Board (hereinafter the "Board");

እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፰.<u>የቦርዱ አባላት</u>**

የቦርዱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ፣ ከእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር፣ ከእንስሳት ምርምር ተቋማት፣ አግባብ ካላቸዉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣የብዝሃህይወት ኢንስቲቲዩት፣ሌሎች ባለድርሻ አካላት እና የሙያ ማህበራት የተውጣጡ ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሰየሙ ይሆናል፡፡

**፱.<u>የአማካሪ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ቦርዱ ሌሎች ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን ጨምሮ በሚከተሉት ላይ ኢንስቲትዩቱን ያማክራል፡-

፩/ በብሔራዊ የርቢ ፖሊሲ፣ የዝርያ ማሻሻያ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች፣ የአፈጻጸም መመሪያዎች ዝግጅትና አፈጻጸም፤

፪/ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት ወደ ሀገር ማስገባት፣ ማላመድ፣ ሀገር ውስጥም ማምረት፣ ማባዛት፣ ሥርጭትና ስርፀት፤

፫/ ሀገር በቀል እና የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች ልየታ፣ መረጣ፣ ብዜት እና ምዝገባ እንዲሁም አጠቃቀም፤

፬/ በእንስሳት ሀብት ዝውውር፣ ልውውጥና አጠቃቀም እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር::

**፲.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ ቦርዱ የሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንስቲቲዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን የኢንስቲቲዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃለይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የ? ??? ? ?? ን ሠራተኞችን በፌደራል ፐብሊክ ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣ በመንግሥት ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደርጉ ግንኙነቶች ሁሉኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የየሦስት ወር እና ዓመታዊ የሥራ ክንውንና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ል፤

፲ሺ፷፭

ሰ) በኢንስቲትዩቱ የሚካሄደውን የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች

2 / A Director General and Deputy Director Generals, as may be necessary, to be appointed by the Government;

3/ The necessary staffs.

**8. <u>Members of the Board</u>**

Members of the Board, including the chairperson, shall be drawn from Ministry of Livestock and Fisheries, livestock research institutions, higher education institutes, biodiversity institute, other stake holders and professional associations and nominated by the Minister and be assigned by the Government; and their number shall be determined as appropriate.

**9.<u>Duties and responsibilities of the Board</u>**

The Board shall advice the Institute, among other strategic issues, on the following matters:

1/ On national breeding policy, breeding improvement programs, strategy and implementations guidelines;

2/ Importation of quality breed improvement inputs, adaptation, domestic production, multiplication and dissemination;

3/ Domestic and improved animal breeds characterization, selection, multiplication, registration and utilization;

4/ On animal resources movement, exchange and utilization; and on the implementation of international agreements.

**10<u>. Duties and responsibilities of the Director General</u>**

1/ The Director General shall, subject to the general direction of the Board, be the chief executive officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without the prejudice to the generality of sub article (1) of this Article, the Director General shall:-

a) Exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) Employ and administer employees in accordance with the federal civil service laws;

c) Prepare and submit annual plan and budget of the Institute to the Ministry and implement same upon approval by the Government;

d) Effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) Represent the Institute in all its dealings with third party;

f) Prepare and submit to the Ministry the quarterly and annual performance and financial reports of the Institute;

ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ውጤታማ እንዲሆን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮችና ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፩. የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣን እና ተግባራት**

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፡-

፩/ በኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር መሠረት የሚመደቡበትን የሥራ ዘርፍ ይመራሉ፣ ያስተዳድራሉ፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጧቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፤

፫/ ተለይቶ ካልተወከለ በስተቀር ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዳይሬክተሩን ተክቶት ይሠራል፡፡

**፲፪ .በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፤

፩/ በመንግሥት ከሚመደብ በጀት እና

፪/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከውስጥ አገልግሎት ከሚሰበሰብ ገቢ፡፡

**፲፫ .የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በፌደራል ዋና ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**፲፬.መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን**

ኢንስቲትዩቱ ስለ እንስሳት ሀብት አጠቃቀምና ብሔራዊ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፡፡

**፲፭.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፲፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ኃይለማሪያም ደሳለኝ**

**ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

g) Plan and organize capacity building programs of the institute, monitor and follow up its success;

3/ The Director General may delegate part of his duties and responsibilities to the deputy Director Generals or employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

**11.Power and Duties of Deputy Director Generals**

The Deputy Director Generals of the Institute:

1 / Direct and administer the department assigned to them in accordance with the institute's organizational structure;

2/ Perform tasks assigned to them by the Director General;

3/ Unless the Director General delegates otherwise, the senior Deputy Director General shall act on behalf of the Director General in his absence.

**12.Budget**

The budget of the Institute shall be drawn from the following sources:

1/ Budget allocated by the Government;

2/ Money from internally collected fees, as permitted pursuant to the directives of the Ministry of Finance and Economic Cooperation.

**13.Books of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of account.

2/ The Institute's books of account and financial documents shall be audited annually by the Federal Auditor General or an auditor to be assigned by the Federal Auditor General.

**14.Power to Issuance of Directives**

The Institute shall Prepare national animal genetic improvement directives and submit to the Ministry and implement same upon approval.

**15.Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazetee.

**Done at Addis Ababa, this 20th Day of January, 2018.**

**HAILEMARIAM DESSALEGNE**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ ፈቃድ | ዕድሳት | ምትክ ፈቃድ |
| 1 | የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2 | የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3 | የአገር ውስጥ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 650 | 550 | 450 |
| 4 | የሥራ ውል ማጽደቂያ | 500 | | |

## SCHEDULE OF FEES

| No. | Types of Services | Amount of Fee (Birr) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | For New License | For Renewal of License | For Replacement of License |
| 1. | Issuance of Work Permit for Foreigners | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2. | Issuance of Overseas Private Employment Agency License | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3. | Issuance of Local Private Employment Agency License | 650 | 550 | 450 |
| 4. | Approval of Contract of Employment | 500 | | |